የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የማዕድን የነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ሚኒስቴር
FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
MINISTRY OF MINES, PETROLEUM AND NATURA GAS

ቀን 14 ህዳር 2010
Date
ቁጥር ሐ01/02/46
Ref.No.

በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
ለአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት
<u>አዲስ አበባ</u>

**ጉዳዩ: <u>በማዕድን ዘርፍ የተሠማሩ ባለሀብቶች የቀረጥ ነጻ አፈቃቀድን ይመለከታል፡፡</u>**

ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤታችሁ ጥቅምት 16 ቀን 2010 ዓ.ም በቁጥር አቃ123/መ/0/29 በተጻፈ ደብዳቤ በማዕድን ዘርፍ ለተሠማሩ ባለሀብቶች በአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት ይሰጥ የነበረው የቀረጥ ነጻ መብት ፈቃድ አገልግሎት ከሰኔ 30 ቀን 2009 ዓ.ም ጀምሮ የተቋረጠ መሆኑን፤ በዘርፉ የተሠማሩ ባለሀብቶች ከማዕድን የነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ሚኒስቴር ወይም ከክልሎች በዘርፉ የቀረጥ ነጻ መብት የመፍቀድ ሥልጣን ካላቸው የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሚጻፍላቸው የቀረጥ ነጻ መብት ደብዳቤዎች አገልግሎት እንዲሰጣቸው ማሳወቃቸውን፤ ነገር ግን የተለያዩ መሥሪያ ቤቶች የቀረጥ ነጻ መብቱን እየጻፉ ስለሆነና ለአፈጻጸም እያስቸገረ ሰለሆነ ክልልም ሆነ የከተማ አስተዳደሮች ለዘርፉ የቀረጥ ነጻ መብት የመፍቀድ ሥልጣን ያላቸውን የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ዝርዝር እንድናሳውቃችሁ መጠየቃችሁ ይታወሳል፡፡

በዚህም መሠረት በፌደራል፣ በክልል ወይም በከተማ አስተዳደር የቀረጥ ነጻ መብት የመፍቀድ ሥልጣን የተሰጠው የማዕድን ፈቃድ እንዲሰጥ በሕግ ሥልጣን የተሰጠው አካል ሲሆን በሕጉ ውስጥ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን እየተባለ የሚጠራው አካል ይሆናል፡፡ ፈቃድ ሰጪው ባለሥልጣን ደግሞ እንደ ነገሩ ሁኔታ የፌደራል፣ የክልል ወይም የከተማ አስተዳደር ሊሆን ይችላል፡፡ በመሆኑም የማዕድን ፈቃድ ለመስጠትና የቀረጥ ነጻ መብትን ለመፍቀድ ሥልጣን የተሰጣቸው አግባብ ያላቸው የፌደራል፣ የክልል ወይም የከተማ አስተዳደር አካላት ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ሲሆኑ ከእነዚህ አካላት ውጭ ያሉት የቀረጥ ነጻ መብትን የመፍቀድ ሥልጣን አልተሰጣቸውም፡፡ በመጨረሻ በማዕድን ዘርፍ የቀረጥ ነጻ መብት የመፍቀድ ሥልጣን የተሰጣቸው አካላት የሚከተሉት መሆናቸውን እንገልጻለን፡፡

| ተ.ቁ | አግባብ ያለው የፌደራል/የክልል/የከተማ አስተዳደር ቢሮ/ኤጀንሲ/ጽሕፈት ቤት |
|---|---|
| 1. | የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የማዕድን፣ የነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ሚኒስቴር |
| 2. | በትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የማዕድንና ኢነርጂ ኤጀንሲ |
| 3. | በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የማዕድንና ኢነርጂ ሀብት ልማት ጽሕፈት ቤት |

☎ : (251-11-)667 55 82
Fax : +(251-11-)6463364,6463426
Addis Ababa Ethiopia

| | |
|---|---|
| 4. | በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የማዕድን ሀብት ልማት ማስፋፊያ ኤጀንሲ |
| 5. | በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የውኃ፣ ማዕድንና ኢነርጂ ቢሮ |
| 6. | በሱማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የአካባቢ ጥበቃ፣ ደን፣ ማዕድንና ኢነርጂ ልማት ኤጀንሲ |
| 7. | በቤንሻንጉል ጉሙዝ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የማዕድን ሀብት ልማት ኤጀንሲ |
| 8. | በደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግሥት የማዕድንና ኢነርጂ ኤጀንሲ |
| 9. | በጋምቤላ ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የውኃ፣ ማዕድንና ኢነርጂ ሀብት ልማት ቢሮ |
| 10. | በሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የኢንቨስትመንት፣ ማዕድንና ኢነርጂ ጽሕፈት ቤት |
| 11 | በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን |
| 12. | በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር የግብርና፣ ውኃ፣ ማዕድንና ኢነርጂ ቢሮ |

ከሠላምታ ጋር